ወእትሐሠይ፡ በአምላኪየ፡ ወመድኃኖየ፤

በፈጣሪዬ፡ በመድኃኒቴ፡ አምኜ፡ ደስ፡ ይለኛል፤

፲፱፤ እግዚአብሔር፡ አምላኪየ፡ ወኃይልየ፡ ዘይሠርዖን፡ ለእገርየ፡ ወለፍጻሜየ፤

እግሮቼን፡ ፈጽሞ፡ የሚሠራራቸው፡ ኃይሌ፡ ፈጣሪዬ፡ እግዚአብሔር፡ ነው፤

ወያቀውመኒ፡ ውስተ፡ መልዕልት፡

በልዕልናም፡ ያጸናኛል፤

ወዲበ፡ ልዑላት፡ ያጼዕነኒ፤

በኃያላኑ፡ ላይ፡ ያሰለጥነኛል፤ አንድም፡ ከሚጠት፡ በኋላ፡ ድንበር፡ ለይልን፡ እያሉ፡ እየተሸከሙ፡ ይወስዱት፡ ነበርና፤

ከመ፡ እማዕ፡ በመኃልይሁ፤

በፍኖቱ፡ ሲል፡ ነው፤ በሕጉ፡ ጸንቼ፡ ጠላቴን፡ ድል፡ እነሳ፡ ዘንድ፡ የሚያሰለጥነኝ፡ እሱ፡ ነው፤

ተፈጸመ፡ ዘዕንባቆም፡ ነቢይ፡ በረከተ፡ አምላኩ፡ የሃሉ፡ ምስሌነ፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፤

አነሳስቶ፡ ለአስጀመረን፡ አስጀምሮ፡ ለአስፈጸመን፡ ለእግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግባው፡ አሜን፡ በእውነት።

ፀሐፊት ሪታና ቤተሰቡ
የግል ቤተ መጻሕፍት

ዘሶፎንያስ ነቢይ፤

መቅድም

ሶፎንያስ፡ ማለት፡ ሰፋኒ፤ ሰፋን፡ ማለት፡ ነው፤ አንድም፡ ቀዳሲ፡ ሥሉጥ፡ ማለት፡ ነው፤ ነገዱ፡ ከነገደ፡ ንፍታሌም፡ ነው፤ መነሣቱ፡ በኢዮስያስ፡ ዘመን፡ ነው፤ እናቱ፡ ንህባ፡ ትባላለች፤

ምዕራፍ ፩

፩፤ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኮነ፡ ኀበ፡ ሶፎንያስ፡ ወልደ፡ ኩሲ፡ ወልደ፡ ጎዶልያ፡ አሞራዊ፤

ዘመጽአ፡ ዘተነግረ፡ ሲል፡ ነው፤ የጎዶልያ፡ ልጅ፡ ከሆነ፡ ከኩሲ፡ ልጅ፡ ከሶፎንያስ፡ ዘንድ፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ ሰብአ፡ አሞርዮን፡ በጠፉበት፡ ወራት፡ ስለተወለደ፡ አሞራዊ፡ አለ፤

ዘሴዴቅያስ፤

የሴዴቅያስ፡ ወገን፡ ከሚሆን፤

በመዋዕለ፡ ኢዮስያስ፡ ወልደ፡ አሞጽ፡ ንጉሠ፡ ይሁዳ፤

በይሁዳ፡ ንጉሥ፡ በአሞጽ፡ ልጅ፡ በኢዮስያስ፡ ዘመን፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ ይህ፡ አርእስት፡ ነው፤ ሠለስቱ፡ ምዕት፡ ለመጻሕፍት፡ አርእስት፡ ሲሠጡ፡ አርእስት፡ ሰጥተውታል፤ እርሱ፡ ግን፡ ነገሩን፡ ሐሊቀ፡ የሐልቁ፡ ብሎ፡ ያመጣዋል፤

፪፤ ሐሊቀ፡ የሐልቁ፡ እምገጸ፡ ምድር፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

ደርሶ፡ ያረዳል፤ እግዚአብሔር፡ ከዚህ፡ ዓለም፡ ፈጽመው፡ ይጠፋሉ፡ አለ፤

፫፤ የሐልቁ፡ ሰብእ፡ ወእንስሳ፤

ሰውም፡ ከብቱም፡ ያልቃሉ፤

ወየሐልቁ፡ አዕዋፈ፡ ሰማይ፡ ወዓሣተ፡ ባሕር፤

የሰማይ፡ ወፎች፡ የባሕር፡ አሣዎች፡ ይጠፋሉ፤ ድርቅ፡ የማያስተባብረው፡ የለምና፤ አንድም፡ መኳንንት፡ መሳፍንት፡ ይጠፋሉ፤

ወይደክሙ፡ ኃጥአን፤

አሥሩ፡ ነገድ፡ በጎዳና፡ ይደክማሉ፤

ወአጠፍዖሙ፡ ለአማፅያን፡ እምገጸ፡ ምድር፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ ከምድር፡ አጠፋቸዋለሁ፡ አለ፤

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

፬፤ ወእነሥእ፡ እዴየ፡ ላዕለ፡ ይሁዳ፡ ወላዕለ፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ኢየሩሳሌም፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

በይሁዳና፡ በኢየሩሳሌም፡ በሚኖሩ፡ ሰዎች፡ እጄ፡ መዓቴን፡ አመጣለሁ፡ ኦለ፡ እግዚአብሔር፤

ወእሥዕር፡ እምዝንቱ፡ ብሔር፡ አስማቲሆሙ፡ ለበዓሊም፤

በዓል፡ ያለውን፡ በዓሊም፡ ብሎ፡ አበዛ፤ የጣዖታቱን፡ ስም፡ ከኢየሩሳሌም፡ አጠፋለሁ፤

ወአስማቲ፡ ማርያን፤

የሚርተኞችን፡ ስም፡ አጠፋለሁ፤

፭፤ ወለእለ፡ ይሰግዱ፡ ለከዋክብቲ፡ ሰማይ፡ በአንሕስት፤

በግምብ፡ ሆነው፡ ለሰማይ፡ ከዋክብት፡ የሚሰግዱትን፡ አጠፋቸዋለሁ፤

ወእለ፡ ይምሕሉ፡ በስመ፡ እግዚአብሔር፡ ንጉሦሙ፡ በሐሰት፤

ንጉሣቸው፡ የሚሆን፡ የእግዚአብሔርን፡ ስም፡ በሐሰት፡ ጠርተው፡ የሚምሉትን፡ ሰዎች፡ አጠፋቸዋለሁ፤

፮፤ ወእለ፡ ይትገኃሡ፡ እምእግዚአብሔር፤

ከእግዚአብሔር፡ የማርቁትን፤

ወእለ፡ ኢይትኤዘዙ፡ ለእግዚአብሔር፤

ለእግዚአብሔር፡ የማይታዘዙትን፡ አጠፋቸዋለሁ፤

፯፤ ፍርሁ፡ እምቅድመ፡ ገጹ፡ ለእግዚአብሔር፡ አምላክ፤

ፈጣሪ፡ ከሚሆን፡ ከእግዚአብሔር፡ ከገጸ፡ መዓቱ፡ የተነሣ፡ ፍሩ፤

እስመ፡ አልፀቀት፡ ዕለተ፡ እግዚአብሔር፤

እስራኤል፡ የሚማረኩባት፡ ቀን፡ ደርሳለችና፤

እስመ፤ አስተዳለወ፡ እግዚአብሔር፡ መሥዋዕቶ፤

እግዚአብሔር፡ መዓቱን፡ መቅሠፍቱን፡ አዘጋጅቷልና፤

ወቀደሶሙ፡ ለኅሩያኒሁ፤

ለጥፋት፡ የተመረጡትን፡ በሞት፡ ለያቸው፤ መቅሠፍቱን፡ መሥዋዕት፡ አለው፤ መሥዋዕት፡ ደስ፡ እንዲያሰኝ፡ መቅሠፍቱም፡ ደስ፡ ያሰኛልና፡ መሥዋዕተ፡ እግዚአብሔር፡ በባሦር፡ እንዲል፤ አንድም፡ ጥምቀትን፡ አዘጋጅቷልና፤ ለጥሙቃኒሁ፡ ሲል፡ ነው፤ የተጠመቁትን፡ ከሀገራቸው፡ ለየቻቸው፡

፰፤ ወይከውን፡ በዕለተ፡ መሥዋዕቱ፡ ለእግዚአብሔር፤

መዓቱን፡ በሚያደርግበት፡ በዔዋዌ፤ አንድም፡ በዕለተ፡ ዓርብ፡ ያደርጋል፤

ወእትቤቀሎሙ፡ ለመላእክት፡ ወለቤተ፡ ንጉሥ፤

አለቆችን፡ የንጉሥን፡ ወገኖች፡ ተበቅዬ፡ አጠፋቸዋለሁ፤ አንድም፡ ሊቃነ፡ አጋንንትን፡ ሠራዊተ፡ አጋንንትን፡ ተበቅዬ፡ አጠፋቸዋለሁ፤

ወለኵሎሙ፡ እለ፡ ይለብሱ፡ አልባሰ፡ ነኪር፤

ሀብተ፡ አጋንንት፡ ያደረባቸው፡ ካህናተ፡ ጣዖቱን፡ ሁሉ፡ አጠፋቸዋለሁ፤

፱፤ ወእትቤቀሎሙ፡ ለኵሎሙ፡ ገሃደ፡ በውስተ፡ አናቅጽ፤

ሁሉንም፡ በአደባባይ፡ ተበቅዬ፡ አጠፋቸዋለሁ፤

ውእተ፡ አሚረ፡ እለ፡ ይመልዑ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኮሙ፡ ዓመፃ፡ ወጽልሁተ፤

ያንጊዜ፡ በደልን፡ ተንኮልን፡ ለቤተ፡እግዚአብሔር፡ የሚመሉ፡ ናቸው፤

፲፤ ወይከውን፡ ይእተ፡ ዕለተ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

የን፡ ጊዜ፡ እንዲህ፡ ይሆናል፡

አለ፤

ወይከውን፡ ቃለ፡ ዓውያት፡ እምአናቅጽ፡ ወእምእለ፡ ይወግዑ፡ በውውዓ፡ እምውስጥ፤

እምእለ፡ ይወግዑ፡ በአናቅጽ፡ ይከውን፡ ቃለ፡ ዓውያት፡ እምውስጥ፡ ሲል፡ ነው፤ በአደባባይ፡ ከሚዋጉ፡ ሰዎች፡ የተነሣ፡ በውስጥ፡ ልቅሶ፡ ይሰማል፤ አንድም፡ ከሚዋጉ፡ ሰዎች፡ የተነሣ፡ በውስጥም፡ በአፍአም፡ ልቅሶ፡ ይሰማል፤

ወቀትል፡ ዓቢይ፡ በውስተ፡ ወግር፤

በኮረብታው፡ ጽኑ፡ ሰልፍ፡ ይደረጋል፤

፲፩፤ ብክዩ፡ እለ፡ ትነብሩ፡ ውስተ፡ ቀትል፤

በሰልፍ፡ ያላችሁ፡ ሁሉ፡ አልቅሱ፤

እስመ፡ ይመስሉ፡ ኵሉ፡ አሕዛበ፡ ከነዓን፡

ሁሉም፡ በጥፋት፡ በግብራቸው፡ ኢያሱ፡ ያጠፋቸውን፡ የከነዓንን፡ ሰዎች፡ ይመስላሉና፤

ወተሠረዉ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ይትዔበዩ፡ በወርቅ፤

በወርቅ፤ አንድም፡ በጣዖት፡ የሚታበዩ፡ ሁሉ፡ ጠፉ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፪፤ ወይከውን፡ ይእተ፡ ዕለተ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር።

ያን፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ እን ዲህ፡ ይሆናል፡ አለ።

እፌትና፡ ለኢየሩሳሌም፡ በማኅቶተ፡ ጥበብ።

ኢየሩሳሌምን፡ በባሕርይ፡ ጥበቤ፡ እየመረመርሁ፡ አጠፋታለሁ።

ወእትቤቀሎሙ፡ ለዕደው፡ እለ፡ ያስተ ሐቅሩ፡ ሕጎሙ፡ እንዘ፡ ይብሉ፡ ኢያ ሤኒ፡ ወኢያኃስም፡ እግዚአብሔር።

እግዚአብሔር፡ ወዳጁን፡ አይጠ ቅምም። ጠላቱን፡ አይጐዳም፡ እያሉ፡ ሕጉን፡ የሚንቁትን። የሚያቃልሉትን፡ ሰዎች፡ ተበ ቅዬ፡ አጠፋቸዋለሁ።

፲፫፤ ወየኃሥር፡ ኃይሎሙ፡ ወይ ትበረበር፡ ቤቶሙ።

ኃይላቸው፡ ይደክማል። ቤታ ቸው፡ ይበዘበዛል።

የሐንፁ፡ ቤተ፡ ወኢይነብሩ፡

ቤት፡ ይሠራሉ። አይኖሩበትም።

ይተክሉ፡ ወይነ፡ ወኢይሰትይዎ።

ወይን፡ ይተክላሉ፡ አይ ጠጡትም።

፲፬፤ እስመ፡ አልፀቀት፡ ዕለተ፡ እግዚአብሔር፡ ዐባይ፡ ቀርበት፡ ወአል ጸቀት፡ ወአፍጠነት፡ ጥቀ፡ ድምፃ፡ ለዕ ለተ፡ እግዚአብሔር፡ መራር፡ ወእኪት።

ዕለተ፡ እግዚአብሔር፡ ዔዋዌ፡

ሐሬር፡ ዔዋዌን፡ የሚያደርግ ባት፡ ቀን፡ ወሬዋ፡ ፈጥኖ፡ ተሰ ምቷልና።

፲፭፤ ፅንዕት፡ ይእቲ።

ጽንዕት፡ ናት።

ዕለተ፡ መንሱት።

የጥፋት፡ ቀን፡ ናት።

ዕለተ፡ ሕማም፡ ወምንዳቤ።

መከራ። ፀዋትወ፡ መከራ፡ የሚ ደረግባት፡ ቀን፡ ናት።

ዕለተ፡ ምምዓ፡ ወሙስና።

ሽብር፡ ጥፋት፡ የሚደረግባት፡ ቀን፡ ናት።

ዕለተ፡ ጽልመት፡ ወቆባር።

ጨለማ፡ ጭጋግ፡ የሚደረግ ባት፡ ቀን፡ ናት።

ዕለተ፡ ደመና፡ ወጊሜ።

ጉም፡ የሚሳብባት። ደመና፡ የተ ረገረገባት፡ ቀን፡ ናት።

፲፮፤ ዕለተ፡ ቀርን፡ ወውውዓ፡ ላዕለ፡ አህጉር፡ ጽኑዓት፡ ወላዕለ፡ በሐው ርት፡ ልዑላት።

ጽኑዓት፡ ልዑላት፡ በሆኑ፡ አገ ሮች፡ ላይ፡ የነጋሪት፡ ድምፅ፡ ድንፋታ፡ የሚሰማባት፡ ቀን፡ ናት።

፲፯፤ ወአመንደቦሙ፡ ለሰብእ፤

ወየሐውሩ፡ ከመ፡ ዕውራን፡ እስመ፡ አበሱ፡ ላዕለ፡ እግዚአብሔር።

እንደ፡ ዕውራን፡ እየዳበሱ፡ ይሄ ዳሉ። እግዚአብሔርን፡ በድለ ዋልና።

ወይክዕዉ፡ ደሞሙ፡ ከመ፡ ማይ።

አሕዛብ፡ የእስራኤልን፡ ደም፡ እንደውሃ፡ አብዝተው፡ ያፈስሱ።

ወሥጋሆሙ፡ ከመ፡ ፀፍዕ።

ሥጋቸውን፡ እንደፈርስ፡ ያደር ጉታል።

፲፰፤ ወኢያድኅኖሙ፡ እንከ፡ ወር ቆሙ፡ ወብሩሮሙ፡ እምዕለተ፡ መዓቱ፡ ለእግዚአብሔር።

እግዚአብሔር፡ መዓቱን፡ መቅ ሠፍቱን፡ ከሚያመጣበት፡ ቀን፡ ወርቃቸው፡ ብራቸው፡ አያድ ናቸውም።

ወእምዕለተ፡ ቅንዓቱ፡ ትጠፍዕ፡ ኵላ፡ ምድር።

ለአምላክነቱ፡ ቀንቶ፡ ከሚያመ ጣው፡ መቅሠፍት፡ የተነሣ፡ ምድር፡ ትጠፋለች።

እስመ፡ ፍጡነ፡ ያሐልቆሙ፡ ለእለ፡

ምዕራፍ፡ ፪

፩፤ ተጋብኡ፡ ወተጋነዩ፡ ሕዝብ፡ አብዳን።

ሰነፎች፡ ወገኖች፡ ተሰብስባችሁ፡ እግዚአብሔርን፡ ተለማመጡ፡ ለምኑ።

፪፤ ዘእንበለ፡ ትኩኑ፡ ከመ፡ ጽጌ፡ ይቡስ፡ ዘወድቀ፡ እምከተማሁ።

ከጫፉ፡ እንደወደቀ፡ አበባ፡ ሳት ሆኑ፡ ለምኑ።

ዘእንበለ፡ ትብጻሕክሙ፡ ዕለተ፡ መዓቱ፡ ለእግዚአብሔር።

እግዚአብሔር፡ የሚፈርድባት፡ ቀን፡ ሳትደርስባችሁ፡ ለምኑ።

፫፤ ኅሥዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ኵል ክሙ፡ ትሑታነ፡ ምድር።

ተዋርዳችሁ፡ የምትኖሩ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ እግዚአብሔርን፡ በሕግ፡ በአምልኮት፡ ፈልጉት።

ተገበሩ፡ ጽድቀ።

ዘጠኙን፡ ሕግጋት፡ ያዙ።

ወኅሥዋ፡ ለርትዕ።

ኢታምልክን፡ ሿት።

ወአውሥእዋ።

ተጨዋወቷት።

ከመ፡ ትድኃኑ፡ እምዕለተ፡ መዓቱ፡ ለእግዚአብሔር።

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

፬፤ እስመ፡ ትትበረበር፡ ጋዛ፡ ወትጠፍዕ፡ አስቀሎና፤

ጋዛ፡ ትበዘበዛለችና፡ አስቀሎናም፡ ትጠፋለችና፤

ወይገፈትዕዋ፡ ለአዛጦን፡ ቀትረ፤

አዛጦን፡ በአፍላ፡ ባለጸግነት፡ ተይዛ፡ ሳለች፡ ትጠፋለች፤

ወይሤርውዋ፡ ለአቃሮን፤

አቃሮንንም፡ ያጠፏታል፤

፭፤ አሌ፡ ሎሙ፡ ለፈላስያን፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ጥቃ፡ ባሕር፡ ፈላስያን፡ ቀርጤ፤

ከቀርጤ፡ ተሰደው፡ መጥተው፡ በደሴት፡ የሚኖሩ፡ ሰዎች፡ ወዮላቸው፤

ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ላዕሌክሙ፡ ምድረ፡ ኢሎፍሊ፤

በኢሎፍሊ፡ የምትኖሩ፡ ሰዎች፡ የእግዚአብሔር፡ ትእዛዙ፡ በናንተ፡ ላይ፡ ነው፤

ወያጠፍዓክሙ፡ እምነ፡ በሐውርቲክሙ፤

ከሀገራችሁ፡ ያጠፋችኋል፤

፮፤ ወትከውን፡ ቀርጤ፡ ቢያተ፡ መራዕይ፡ ወመራዕየ፡ አባግዕ፤

ቀርጤ፡ ተፈታ፡ የከብት፡ የበግ፡ መሠማሪያ፡ ትሆናለች፤

፯፤ ወይከውን፡ በሐውርት፡ ብሔር፡ ለተረፈ፡ ይሁዳ፤

አገሩ፡ ሁሉ፡ አሥሩ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ ለቀሩት፡ ለሁለቱ፡ ነገድ፡ ይሆናሉ፤

ወይትረአይዎሙ፡ በውስተ፡ አብያቲሆሙ፤

ትሩፋን፡ የአሕዛብን፡ ቤት፡ ይወርሳሉ፤

አስቀሎናሰ፡ ድንገቴሆሙ፡ ይነብሩ፡ እምቅድመ፡ ገጸሙ፡ ለደቂቀ፡ ይሁዳ፤

የአስቀሎና፡ ሰዎች፡ ግን፡ ከይሁዳ፡ ልጆች፡ ፊት፡ የተነሣ፡ ደንግጠው፡ ይኖራሉ፤

እስመ፡ ተሣሃሎሙ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኮሙ፤

ፈጣሪያቸው፡ እግዚአብሔር፡ ይቅር፡ ብሏቸዋልና፤

ወሜጠ፡ ዔዋሆሙ፤

ምርኳቸውን፡ መልሷልና፤

፰፤ ወሰምዐ፡ እግዚአብሔር፡ ዕዕለተ፡ ሞዓብ፤

እግዚአብሔር፡ የሞዓብን፡ ስድብ፡ ሰማ፤

ወኩርዓቶሙ፡ ለደቂቀ፡ አሞን፤

የአሞንን፡ ልጆች፡ ትዕቢታቸውን፡ ሰማ፤ አንድም፡ ድኃ፡ መቀጥቀጣቸውን፡ ሰማ፤

ዘከመ፡ አኅሠርዎሙ፡ ለሕዝብየ፤

ወገኖቼን፡ እንዳዋረዷቸው፡ ሰማ፤

ወተዘኃሩ፡ ላዕለ፡ ብሔርየ፤

በሀገሬ፡ እ[illegible]

፱፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ሕያው፡ አነ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ኃያል፡ አምላከ፡ እስራኤል፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ ኃያል፡ የሚሆን፡ የእስራኤል፡ ፈጣሪ፡ እግዚአብሔር፡ ሕያው፡ ነኝ፡ ማለት፡ አጠፋችኋለሁ፡ አለ፤

እስመ፡ ሞዓብኒ፡ ከመ፡ ሰዶም፡ ትከውን፤

ሞዓብ፡ እንደ፡ ሰዶም፡ ትሆናለችና፤

ወደቂቀ፡ አሞንኒ፡ ከመ፡ ገሞራ፤

የአሞንም፡ ልጆች፡ እንደገሞራ፡ ይሆናሉና፤

ወደማስቆኒ፡ ተሐልቅ፡ ከመ፡ ክምረ፡ ዕክል፡ ወትማስን፡ ለዓለም፤

ደማስቆም፡ የተከመረውን፡ እህል ወራሪ፡ ዘራፊ፡ ተነጣጥቆ፡ እንዲያጠፋው፡ ለዘለዓለሙ፡ ትጠፋለች፤

ወእለ፡ ተርፉ፡ ሕዝብየ፤ ይበረብርዎሙ፡ ወይወርስዎሙ፤

አሥሩ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ የቀሩ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ይበዘብዟቸዋል፤ ይወርሷቸዋል፤

፲፤ ወዛቲ፡ ትከውኖሙ፡ ህየንተ፡ ፅዕለቶሙ፤

ይህች፡ ጥፋታቸው፡ ስለ፡ ስድ[illegible]ዮለች፤

እስመ፡ አመ፡ ነስሑ፡ እምዝ፡ ተዓበዩ፡ ላዕለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

እስመና፡ አመ፡ አንድ፡ ጊዜ፡ አይወጣም፤ ሁሉን፡ በሚገዛ፡ በእግዚአብሔር፡ ላይ፡ ከሚታበዩት፡ ትዕቢት፡ በተመለሱ፡ ጊዜ፡ ትከውኖሙ፡ ላለው፤ አንድም፡ በእግዚአብሔር፡ ከታበዩት፡ ከትዕቢታቸው፡ ቢመለሱ፡ ይቅር፡ ይላቸዋልና፡ ትከውኖሙ፡ ላለው፤

፲፩፤ ወያመጽእ፡ እግዚአብሔር፡ ላዕሌሆሙ፡ መዓተ፤

ባይመለሱ፡ ግን፡ እግዚአብሔር፡ መቅሠፍት፡ ያመጣባቸዋል፤

ወይሤርዎሙ፡ ለኵሎሙ፡ አማልክተ፡ አሕዛበ፡ ምድር፤

የአሕዛብን፡ ጣዖታት፡ ከዚህ፡ ዓለም፡ ያጠፋቸዋል፤

ወይሰግዱ፡ ሎቱ፡ ኵሎሙ፡ በበበሐውርቲሆሙ፤

ሁሉም፡ በየሀገራቸው፡ ይሰግዱለታል፤

ወኵሉ፡ ደሴተ፡ አሕዛብ፤

ነገሥተ፡አሕዛብ፡ይሰግዱለታል፤

፲፪፤ ወአንትሙሂ፡ ኢትዮጵያ፡ ቅቱላን፡ በኲናት፡ አንትሙ፤

እናንተ፡ የኢትዮጵያ፡ ሰዎች፡ እናንተም፡ በጦር፡ ትጠፋላችሁ፤

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

፲፫፤ ወአነሥእ፡ እዴየ፡ ላዕለ፡ ሰሜን፤

እደ፡ መዓቴን፡ በባቢሎን፡ አነሣለሁ፤

ወአጠፍዖሙ፡ ለፋርስ፤

የፋርስንም፡ ሰዎች፡ አጠፋ ቸዋለሁ፤

ወእሬስያ፡ መዝበረ፡ ለነነዌ፤

ነነዌንም፡ የተፈታች፡ አደር ጋታለሁ፤

ወከመ፡ በድው፡ ዘአልቦ፡ ማይ፤

ውሀ፡ እንደሌለበት፡ ምድረ፡ በዳ፡ አደርጋታለሁ፤

፲፬፤ ወይትረዓዩ፡ መራዕይ፡ በማዕከላ፤

በመካከሏም፡ ብዙ፡ የከብት፡ መንጋ፡ ይሰማሩባታል፤

ወኵሉ፡ አርዌ፡ ገዳም፤

የምድረ፡ በዳ፡ አውሬ፡ ሁሉ፡ ይኖሩባታል፤

ወይነብሩ፡ አቃርብት፡ ውስተ፡ ዔዖታ፤

ጊንጦችም፡ በመስኳ፡ ይኖራሉ፤

ወይነቅዉ፡ አራዊተ፡ ገዳም፡ በውስተ፡ አፍላጊሃ፤

የምድረ፡ በዳ፡ አራዊቶችም፡ በወንዟ፡ ይጮሃሉ፤

ወቆዓት፡ ውስተ፡ አናቅጺሃ፤

ቁራዎችም፡ በአደባባይዋ፡ ይጮሃሉ፤

፲፭፤ እስመ፡ ከመ፡ አርዝ፡ ኑኃ፡ ለዛቲ፡ ሀገር፡ ዓማፂት፡ እንተ፡ ትነብር፡ ተአሚና፤

ጠላት፡ ጠፍቶላት፡ በጤና፡ የም ትኖር፡ አመፀኛ፡ የምትሆን፡ የነነዌ፡ ገናንነትዋ፡ እንደ፡ ደጋ፡ ዛፍ፡ ነበርና፤

እንዘ፡ ትብል፡ በልባ፡ አነ፡ ይእቲ፤

በልቧ፡ እመቤት፡ እኔ፡ ብቻ፡ ነኝ፡ የምትል፤

ወአልቦ፡ እንተ፡ ከማየ፤

እንደኔ፡ ያለ፡ እመቤት፡ የለም፡ የምትል፤

እፎ፡ እንከ፡ ማሰነት፤

እንዲህ፡ የምትል፡ ነነዌ፡ እን ዴት፡ ጠፋች? እንድትባል፡ አደ ርጋታለሁ፤

ወኮነት፡ ምርዓየ፡ ለአርዌ፡ ገዳም፤

ለአራዊትም፡ መሰማሪያ፡ እን ዴት፡ ሆነች፡ እንዲሏት፡ አደ ርጋለሁ፤

ወኵሉ፡ እንተ፡ ላዕሌሃ፡ የሐልፍ፡ ይትፋፀይ፤

በሷ፡ ላይ፡ የሚሄድ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ ያ[illegible]

ይሰማኛል፤ ብሎ፤ አንድም፡ እን ዴት፡ ጠፋች፡ ብሎ፤ በአንክሮ፤ አንድም፡ ፈርቶ፤

ወይጠፍሕ፡ እደዊሁ፡ እንዘ፡ ይብል፤

እጁንም፡ ያጨበጭባል።

ምዕራፍ ፫

፩፤ ወይብል፡ ኦ፡ ላህይት፡ ወሠ ናይት፡ ርግብ፡ ሀገር፡ እንተ፡ ኢትሰ ምዕ፡ ወኢትትዌከፍ፡ ተግሣጸ፤

ደመ፡ ግቡ፡ መልካም፡ ርግብ፡ ነነዌ፡ ያስተማሯትን፡ የማት ሰማ፣ ምክር፡ አዝናትን፡ የማ ትቀበል፤

፪፤ ወኢትትዌከል፡ በእግዚአብ ሔር፡ ወኢቀርበት፡ ኀበ፡ አምላካ፤

በእግዚአብሔር፡ የማታምን፡ ወደ ፈጣሪዋ፡ የማትቀርብ፡ ነነዌ፤

፫፤ መላእክቲሃኒ፡ በውስቴታ፡ ይጥ ኀሩ፡ ከመ፡ አንበሳ፤

አለቆቿ፡ በውስጧ፡ እንደ፡ አን በሳ፡ የሚያናፉ፤

ወአበይቲሃኒ፡ ከመ፡ ተኵላተ፡ ዓረብ፡ እለ፡ ኢያበይቱ፡ ሎሙ፡ ለነግህ፤

መኳንንቷም፡ በምዕራብ፡ እን ዳሉ፡ ለነገ፡ እንደማያሳድሩ፡ ተኵ [illegible]

፬፤ ወነቢያቲሃኒ፡ ዕደው፡ መስተ ዓብዳን፤

ነቢያቶቿም፡ ሰንፈው፡ የሚ ያሰንፉ፡ ናቸው፤

ወካህናቲሃኒ፡ ያረኵሱ፡ መቅደሰ፡ ወየዓልዉ፡ ሕገ፤

ካህናቶቿም፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ ያረክሳሉ፣ ሕገ፡ እግዚአብሔ ርን፡ ያፈርሳሉ፤

፭፤ ወጻድቅሰ፡ በማዕከላ፡ ኢይገ ብር፡ ዓመፃ፤

ጻድቅ፡ ሕዝቅያስ፣ ጻድቅ፡ ዘሩ ባቤል፡ ግን፡ በመካከሏ፡ ክፉ፡ ነገር፡ አያደርግም፤

ከመ፡ በጽባሕ፡ ይሁብ፡ ኵነኔሁ፤

ሚጠትን፡ ፈጥኖ፡ እንደሚያደ ርግ፡ መጠን፤ አንድም፡ ኦሪ ትን፡ እንደሚያስተምር፡ መጠን፡ እግዚአብሔር፡ ይፈርድስታል፤

ወኢይመውዖ፡ እንከ፡ አማፂ፤

ዓመፀኛ፡ ሰው፡ ድል፡ አይነ ሣውም፤

፮፤ ወነፃሕክዎሙ፡ ለዕቡያን፡ በሞት፤

ትዕቢተኞችን፡ በሞት፣ አጠፋ ኋቸው፤

ወአማሰንኩ፡ በሐውርቲሆሙ፤

አገራቸውን፡ አጠፋሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወአበዲ፡ ፍኖቶሙ፡ ለግሙራ፡ ከመ፡
ኢይክሃሉ፡ ኃሊፈ፡ ውስቴታ፤

በኋ፡ መሄድ፡ እንዳይቻላቸው፡
ጐዳናዋን፡ ፈጽሜ፡ ምድረ፡
በዳ፡ አደርገዋለሁ፤

ወሐልቃ፡ አህጉሪሆሙ፤

አገሮቻቸው፡ ጠፉ፤

ወአልቦ፡ ዘተርፈ፡ ዘይነብሮን፤

በዚያ፡ ለመኖር፡ የቀረ፡ ሰው፡
የለም፤

፯፤ ወዕቤ፡ ፍርሁኒ፡ ወተወከፉ፡
ተግሣጽየ፡ ከመ፡ ኢትሠረዉ፡ እምቅ
ድመ፡ አዕይንትየ፤

ከፊቴ፡ እንዳትጠፉ፡ ፍሩኝ፡ ምክ
ሬንም፡ ተቀበሉ፡ አልሁ፤

ወለኵሉ፡ዘተበቀልክዎ፡ይደሉ፡ይጊሥ፤

ሰባ፡ ዘመን፡ የተበቀልሁት፡ እስ
ራኤልን፡ ለመማረክ፡ ይገሰግስ፡
ዘንድ፡ አሕዛብ፡ ይዘጋጅ፤ አን
ድም፡ ሰባ፡ ዘመን፡ የተበቀልሁት፡
እስራኤል፡ አሕዛብን፡ ለመማ
ረክ፡ ይገሰግስ፡ ዘንድ፡ ይዘጋጅ፤

እስመ፡ ማሰነ፡ ኵሉ፡ ሠርዖሙ፤

ልጆቻቸው፡ ጠፍተዋልና፤

፰፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ተዓገሡኒ፡
እስከ፡ አመ፡ እትነሣእ፡ ይቤ፡ እግዚ
አብሔር፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ በረድኤት፡ እስ
ክነሣ፡ ድረስ፡ ሰባ፡ ዘመን፡
ጠብቁኝ፡ አለ፤

ወከመ፡ እሥዐር፤

አሕዛብን፡ አጠፋ፡ ዘንድ፤ አን
ድም፡ ኢጋንንትን፡ አጠፋ፡ ዘንድ፤

ወከመ፡ እንሣእ፤

እስራኤልን፡ በረድኤት፡ እጠ
ብቅ፡ ዘንድ፤ አንድም፡ ነፍሳ
ትን፡ አወጣ፡ ዘንድ፤

እስመ፡ ኵነኔየ፡ ላዕለ፡ ማኅበረ፡
አሕዛብ፤

ፍርዴ፡ በአሕዛብ፡ ወገኖች፡
ላይ፡ ነውና፤

ከመ፡ ኢይትመየጡ፡ ነገሥት፡ ወዕ
ክዑ፡ ላዕሌሆሙ፡ መቅሠፍተ፡
መዓትየ፤

ነገሥታቱ፡ ወደ፡ ሕይወት፡
እንዳይመለሱ፡ ተቆጥቼ፡ ያመ
ጣሁባቸውን፡ መዓት፡ መቅሠ
ፍት፡ አመጣባችኋለሁ፤

እስመ፡ ታጠፍዕ፡ ለኵላ፡ ምድር፡ እሳተ፡
ቅንዓትየ፤

ለአምላክነቴ፡ ቀንቼ፡ ያመጣኋት፡
መቅሠፍት፡ ዓለሙን፡ ሁሉ፡
ታጠፋለችና፤

፱፤ ወይእተ፡ አሚረ፡ እመይጥ፡
ልሳኖሙ፡ ለኵሎሙ፡ አሕዛብ፡ በመ
ዋዕሊሃ፤

ያን፡ ጊዜ፡ በሚጠት፡ አሕዛብ፡
ሁሉ፡ በአንድ፡ በሕገ፡ ኦሪት፡
ያምናሉ፡ ...

ሐዲስ፡ በሕገ፡ ወንጌል፡ ያም
ናሉ፤ አሕዛብ፡ በሚጠፉበት፡
ወራት፡ የእስራኤልን፡ አንደ
በት፡ ያመሰግኑኝ፡ ዘንድ፡ ወደ፡
ምስጋና፡ እመልሳለሁ፤ አን
ድም፡ ጌታ፡ ሰው፡ በሆነበት፡
ወራት፡ የምእመናንን፡ አንደ
በት፡ ያመሰግኑኝ፡ ዘንድ፡ ወደ፡
ምስጋና፡ እመልሳለሁ፤

ከመ፡ ኵሉ፡ ይጸውዕ፡ ስመ፡ እግ
ዚአብሔር፤

ሰው፡ ሁሉ፡ የእግዚአብሔርን፡
ስም፡ ይጠራ፡ ዘንድ፤

ወከመ፡ ይትቀነዩ፡ ሊተ፡ በ፩ዱ፡
አርዑት፤

በሕገ፡ ኦሪት፡ ይገዛልኛል፤ አን
ድም፡ በሕገ፡ ወንጌል፡ ይገዙ
ልኛል፤

፲፤ እምነ፡ ማዕዶተ፡ ፈለገ፡ ኢት
ዮጵያ፡ ያመጽኡ፡ ሊተ፡ መሥዋዕተ፤

ከኢትዮጵያ፡ ወንዝ፡ ጀምሮ፡
መሥዋዕቱን፡ ያመጡልኛል፤

፲፩፤ ወይእተ፡ አሚረ፡ ኢትትኃ
ፈር፡ እምኵሉ፡ ጌጋይከ፡ ዘአበስከ፡
ሊተ፤

እኔን፡ ከበደልኸኝ፡ በደል፡ የተ
ነሣ፡ ያንጊዜ፡ መከራ፡ መጥቶ
ብህ፡ አታፍርም፤

ይእተ፡ አሚረ፡ አአትት፡ እምኔከ፡ ኃሣ
ረከ፡ ወዕዕለተከ፤

ያንጊዜ፡ ስድብህን፡ ተወርዶ
ህን፡ ከንተ፡ አርቃለሁ፤

ወኢትደግም፡ እንከ፡ አዕብዮ፡ አፉከ፡
ላዕለ፡ ደብረ፡ መቅደስየ፤

ዳግመኛ፡ አንደበትህን፡ ከፍ፡
ከፍ፡ አድርገህ፡ በመመስገኛዬ፡
ቦታ፡ በኢየሩሳሌም፡ አትናገርም፤

፲፪፤ ወአተርፍ፡ ሕዝበ፡ ብዙኀነ፡
ለከ፡ ዘይውህጡከ፤

አንተን፡ የሚያጠፉህ፡ እስራኤ
ልን፡ አስቀራለሁ፤

፲፫፤ ወይፈርሁ፡ ስምየ፡ እለ፡
ተርፉ፡ እምእስራኤል፤

አሥሩ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ የቀሩ፡
ሁለቱ፡ ነገድ፡ ስሜን፡ ይፈራሉ፤

ወኢይገብሩ፡ እንከ፡ ዓመፃ፤

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ክፉ፡ ሥራ፡
አይሠሩም፤

ወኢይነብቡ፡ ከንቶ፤

ከንቱ፡ ነገርን፡ አይናገሩም፤

ወኢይትረከብ፡ ውስተ፡ አፉሆሙ፡
ልሳነ፡ ጽልሑት፤

በአንደበታቸው፡ ክፉ፡ ነገር፡
አይነገርም፤

ወይነብሩ፡ ተአሚኖሙ፡ ወይትርአዩ፤

ጠላት፡ ጠፍቶላቸው፡ በተድላ፡
በደስታ፡ ይኖራሉ፤

ወአልቦ፡ ዘይጌርሞሙ፡ እንከ፤

የሚያስፈራቸው፡ የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬ ተፈሥሒ፡ ወለተ፡ ጽዮን፤
የጽዮን፡ ልጅ፡ ደስ፡ ይበልሽ፤
ወስብኪ፡ ኢየሩሳሌም፡
ኢየሩሳሌም፡ የሚጠትን፡ ነገር፡ ተጨዋወተች፤
ተፈሥሒ፡ ወተሐሠዪ፡ በኵሉ፡ ልብኪ፡ ኢየሩሳሌም፤
ኢየሩሳሌም፡ በፍጹም፡ ልቡናሽ፡ ደስ፡ ይበልሽ፤ አንድም፡ የኦሪት፡ የወንጌል፡ የጥምቀት፡ ልጅ ደስ፡ ይበልሽ፤
እስመ፡ አዕተተ፡ እግዚአብሔር፡ ግፍዓኪ፤
እግዚአብሔር፡ በደልሽን፡ አርቆልሻልና፤ አንድም፡ መርገመ፡ ነፍስን፡ አርቆልሻልና፤
ወባልሐኪ፡ እምእደ፡ እኩይ፤
ከናቡከደነፆር፡ እጅ፡ አዳነሽ፤ አንድም፡ ከዲያብሎስ፡ እጅ፡ አዳነሽ፤
፲፭ ወይነግሥ፡ እግዚአብሔር፡ ማዕከሌኪ፤
እግዚአብሔር፡ በመካከልሽ፡ ነግሦ፡ ይኖራል፤ አንድም፡ እግዚአብሔር፡ በመካከልሽ፡ ይሰቀላል፤
ወኢትሬእዪ፡ እንከ፡ እኪተ፤
እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ዔዋዌን፡ አታዩም፤ አንድም፡ መርገመ፡ ሥጋ፡ አየገኝሽም፤

፲፮ ይእተ፡ አሚረ፡ ይቤላ፡ እግዚአብሔር፡ ለኢየሩሳሌም፡ ጽንዒ፡ ወለተ፡ ጽዮን፤
ያን፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ ኢየሩሳሌምን፡ የጽዮን፡ ልጅ፡ ጽኚ፡ ይላታል፤
ወኢይደክማ፡ እደውኪ፤
ቃልሽ፡ ከመምከር፡ እጅሽ፡ ከመወርወር፡ አይደክምም፤
፲፯ እስመ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክኪ፡ ምስሌኪ፤
እግዚአብሔር፡ በረድኤት፡ ካንቺ፡ ጋር፡ አለና፤
ወውእቱ፡ ይክል፡ አድኅኖተኪ፤
እሱ፡ አንቺን፡ ማዳን፡ ይቻለዋል፤
ወያመጽእ፡ ላዕሌኪ፡ ፍሥሐ፡ ወሐሤተ፤
ተድላውን፡ ደስታውን፡ ያመጣልሻል፤
ወይሄድስኪ፡ በፍቅሩ፤
በፍቅሩ፡ ያጸናሻል፤
ወይትፌሣሕ፡ ብኪ፡ በሐሤት፡ ከመ፡ አመ፡ ዕለተ፡ በዓል፤
በዓለ፡ ፋሲካን እንደምታከብሪበት፡ ጊዜ፡ በአንቺ፡ ደስ፡ ይለዋል፤
፲፰ ወያስተጋብዖሙ፡ ለፃውዋንኪ፤
ምርኮኞችሽን ይሰበስባቸዋል፤

አሌ፡ ሎ፡ ለዘአንሥአ፡ ዕዕለተ፡ ላዕሌኪ፤
በአንቺ፡ ላይ፡ ቃሉን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አድርጎ፡ ለሚናገር፡ ወዮለት፤ አንድም፡ ባንቺ፡ ላይ፡ ክፉ፡ ነገር፡ ለሚናገር፡ ለዲያብሎስ፡ ወዮለት፤
፲፱ ናሁ፡ አነ፡ እገብር፡ በውስቴትኪ፤
እነሆ፡ እኔ፡ ሚጠትን አደርጋለሁ፤
ይእተ፡ አሚረ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ አድኅና፡ ለምንድብት፤
ያን፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤ በመከራ፡ የተጨነቀች፡ ሁለቱን፡ ነገድ፡ አድናታለሁ፤
ወእትዌከፋ፡ ለግድፍት፤
በመከራ፡ የተጣለች፡ አሥሩን፡ ነገድ፡ በረድኤት፡ እቀበላታለሁ፤
ወእሬስዮሙ፡ ስሙያነ፤
ስመ፡ ጥር፡ አደርጋቸዋለሁ፤
ወምክሐ፡ ለኵሉ፡ ምድር፤
በዓለሙ፡ ሁሉ፡ መመኪያ፡ አደርጋቸዋለሁ፤

፳ ወኢይትኃፈሩ፡ ብኪ፡ ይእተ፡ አሚረ፡ አመ፡ አሠነይኩ፡ ለኪ፤
ላንቺ፡ በጎ፡ ነገር፡ ባደረግሁልሽ፡ ጊዜ፡ ያንጊዜ፡ መከራ፡ መጥቶባቸው፡ አያፍሩም፤
ወአመ፡ ተወከፍኩክሙ፤
በረድኤት፡ በተቀበልኋችሁ፡ ጊዜ፤
ወእሬስየክሙ፡ ስሙያነ፡ ወምክሐ፡ ለሕዘቢሃ፤
ለሠራዊቷ፡ መመኪያ፡ ስመ፡ ጥሩዎች፡ አደርጋችኋለሁ፤
አመ፡ ሜጥኩ፡ ዔዋክሙ፡ በቅድሜክሙ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤
ምርኳችሁን፡ በመለስሁ፡ ጊዜ፡ ስመ፡ ጥሩዎች፡ አደርጋችኋለሁ፡ አለ፡ እግዚአብሔር፤
ተፈጸመ፡ ዘሶፎንያስ፡ ነቢይ፡ በሰላመ፡ እግዚአብሔር፡ በረከተ፡ አምላኩ፡ የሃሉ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፤
አነሣስቶ፡ ለአስጀመረን፤ አስጀምሮ፡ ለአስፈጸመን፡ ለእግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይገባው፤ አሜን፡ በውነት።

www.ethiopianorthodox.org